Liberté • Égalité • Fraternité
RÉPUBLIQUE FRANÇAISE

# የፍትህ ሚኒስቴር

# የመብቶች መግለጫ

በቁጥጥር ሰው ለዋለ የሚሰጥ
መደበኛ ህግ (የፈረንሳይ የወንጀል ዳኝነት ህግ አንቀጽ 63 እና 63-1)

**ይህ መረጃ ሊረዱት በሚችሉት ቋንቋ ሊሰጥዎ ይገባል።**
**በህግ ጥላ ስር በሚቆዩበት ግዜ ሁሉ ይህ ዶክመንት ከእርስዎ ጋር ሊቆይ ይችላል።**

በህግ ጥላ ስር የሚገኙት በእስር ሊያስቀጣ የሚችል ወንጀል ፈፅመዋል ወይም ለመፈፀም ሞክረዋል የሚል አንድ ወይም ከዚያ በላይ ጥርጣሬዎች በመኖራቸው ምክንያት መሆኑ ተነግሮዎታል።

ፈፅመዋል ተብለው ስለተጠረጠሩበት ወንጀል አይነት፣ ስለተፈጸመበት ቦታ እና ግዜ፤ እንዲሁም በቁጥጥር ስለዋሉበት ምክንያት የማወቅ መብት አሎት። ስለነዚህ ነገሮች እስከ 24 ሰዓታት ሊቆይ በሚችለው በቁጥጥር ባሉበት ግዜ ውስጥ ይነገርዎታል።

ይህ ግዜ ሲያልቅ የተጠረጠሩበት ወንጀል ቢያንስ አንድ አመት የሚያስከስስ ከሆነ አቃቤ ህግ ወይም ጉዳዩን የሚያየው ዳኛ በቁጥጥር ስር የሚውሉበትን ግዜ ለተጨማሪ 24 ሰዓታት ሊያራዝመው ይችላል። ዳኛው ፈቃዱን ሊሰጥ የሚችለው ፊቱ ከቀረቡ ብቻ ነው።

በህግ ጥላ ስር የሚቆዩበት ግዜ ሲጠናቀቅ በአቃቤ ህግ ወይም ጉዳዩን በሚመለከተው ዳኛ ውሳኔ መሰረት ፍርድ ቤት ሊቀርቡ ወይም ሊለቀቁ ይችላሉ። ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ከሆነ በህግ ጥላ ስር የቆዩበት ግዜ ባለቀ ከ 20 ሰዓታት በማይበልጥ ግዜ ውስጥ ይቀርባሉ።

## በተጨማሪም፤ የሚከተሉት መብቶች እንዳሎት ተነግሮዎታል፦

### ለተወሰኑ ሰዎች ስለሁኔታው ማሳወቅ

አብሮት ለሚኖር ሰው፣ ከወላጅዎ ለአንዳቸው፣ ወይም ከወንድሞችዎ አልያም እህቶችዎ ለአንዳቸው በህግ ጥላ ስር ስላሉበት ሁኔታ በስልክ ማሳወቅ ይችላሉ።

ቀጣሪዎንም ማሳወቅ ይችላሉ።

የውጭ ዜጋ ከሆኑ፤ ለሀገርዎ ቆንጽላ ኃላፊዎች ማሳወቅ ይችላሉ።

ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች ካልኖሩ በስተቀር እነዚህ ጥያቄዎችዎ ባነስዋቸው ከ 3 ሰዓት በማይበልጥ ግዜ ውስጥ ይስተናገዳሉ።

በህግ ከለላ ስር ያሉ ከሆነ፤ ሞግዚትዎ፣ ተገቢው አዋቂ ወይም ባላደራ ስለተወሰዱት እርምጃዎች እንዲያውቅ ይደረጋል።

ሆኖም ግን የማሳወቁ ሂደት መረጃን በመሰብሰብ ወይም በሰው ህይወት፣ ነፃነት ላይ አደጋን የሚፈጥር ከሆነ አቃቤ ህግ ወይም ጉዳዩን የሚመለከተው ዳኛ ሊያዘገየው ወይም ሊያግደው ይችላል።

### ከግለሰብ ጋር ስለመገናኘት

በህግ ቁጥጥር ስር እርስዎ እንደዋሉ ከተነገራቸው ሰዎች ከአንዳቸው ጋር በጽሁፍ፣ ስልክ ወይም ፊት ለፊት ለመገናኘት መጠየቅ ይችላሉ።

ጥያቄዎ በቁጥጥር ስር ከዋሉበት ምክንያት ጋር አብሮ የማይሄድ ከሆነ፤ ወይም ወንጀል እንዲፈጸም መንገድ የሚከፍት ከሆነ መርማሪ ኦፊሰሩ ጥያቄዎን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል። የተጠቀሰው ኦፊሰር ወይም እሱ የሚሾመው ግለሰብ የሚያደርጉት ግንኙነት በእርሱ ቁጥጥር ስር፤ እንዲሁም በምን አይነት ሁኔታ እና ለምን ያህል ግዜ ከ 30 ደቂቃ በማይበልጥ መደረግ እንዳለበት ይወስናል።

### በዶክተር ስለመመርመር

በዶክተር ለመመርመር መጠየቅ ይችላሉ። በህግ ቁጥጥር ስር የሚውሉበት ግዜ ከተራዘመ፤ ድጋሜ በዶክተር ለመምርመር ጥያቄ ማንሳት ይችላሉ።

በህግ ከለላ ስር ያሉ ከሆነ፤ ሞግዚትዎ፣ ተገቢው አዋቂ ወይም ባላደራ የህክምና ምርመራ እንዲደረግሎት ሊጠይቅ ይችላል።

### ቃል መስጠት፣ ጥያቄ መመለስ ወይም ዝም ማለት

ማንነትዎን ካረጋገጡ በኋላ፤ ክስዎ በሚካሄድበት ግዜ የሚከተሉት መብቶች አሎት፦

– ቃል መስጠት
– ለተጠየቁት ጥያቄ ምላሽ መስጠት

– ወይም ዝም ማለት

# የጠበቃ ድጋፍ ስለማግኘት

### የጠበቃ ምርጫ

በቁጥጥር ስር ከዋሉበት ግዜ አንስቶ፣ በክስ ሂደትዎ ግዜ፣ እና በህግ ጥላ ስር የሚቆዩበት ግዜ በተራዘመበት በማንኛውም ግዜ ከመረጡት ጠበቃ ድጋፍ መጠየቅ ይችላሉ። ጠበቃ መቅጠር ካልቻሉ ወይም የመረጡት ጠበቃ ሊገኝ የማይችል ከሆነ ወዲያውኑ ጠበቃ እንዲመደብልዎ መጠየቅ ይችላሉ።

በተጨማሪም ጠበቃዎ ካገኟቸው ሰዎች መካከል በአንዳቸው ሊሾምልዎ ይችላል። ይህ በሚሆንበት ግዜ፤ የጠበቃውን መሾም ማረጋገጥ አለብዎት።

በህግ ከለላ ስር ያሉ ከሆነ፤ ሞግዚትዎ፣ ተገቢው አዋቂ ወይም ባላደራ ጠበቃ ሊሾም አልያም በህግ ባለሙያዎች ፕሬዝዳንት በኩል እንዲሾም ሊጠይቅ ይችላል።

### የህግ ድጋፍ እና የምላሽ ግዜ

የውይይቱን ምስጢራዊነት በጠበቀ መልኩ ጠበቃዎ ለ 30 ደቂቃ ሊያገኝዎ ይችላል። በቁጥጥር ስር የሚውሉበት ግዜ ከተራዘመ፤ ጠበቃዎን በድጋሜ ለማግኘት መጠየቅ ይችላሉ።

በእርስዎ ጥያቄ መሰረት ጠበቃዎ እርስዎ የሚሳተፉባቸውን የክስ ሂደቶች፣ክርክሮች፣ምልልሶች ወይም ማንነትን የመለያ ውይይቶች ላይ መሳተፍ ይችላል።

ይህ በሚሆንበት ግዜ፣ ማንነትዎን ለመለየት ከሚደረጉ ጥያቄ እና መልሶች ውጪ የመጀመሪያ ችሎትዎ ጠበቃዎ ስለ ችሎቱ ከተነገራቸው 2 ሰዓት እስከሚያልፍ ድረስ ጠበቃዎ ባሌሉበት ችሎት አይካሄድም። ነገር ግን የምርመራው ሁኔታ የሚያስገድድ ከሆነ በአቃቤ ህግ ወይም ጉዳዩን በሚያየው ዳኛ ፍቃድ የክስ ሂደትዎ ጠበቃዎ ባሌለበት ወዲያውኑ ሊጀምር ይችላል።

ክስ ማንበብ ወይም ክርክር እየተካሄደ ባለበት ግዜ ጠበቃዎ ከደረሰ፤ ከጠበቃዎ ጋር ይነጋገሩ ዘንድ ሂደቱ እንዲቆምልዎት መጠየቅ ይችላሉ።

ነገር ግን አሳማኝ ምክንያቶች ከኖሩ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤ አቃቤ ህግ፣ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳኛ ወይም የነጻነት እና እስር ዳኛ ክስዎ በሚነበብበት ግዜ 12 ሰዓት ለማይበልጥ ግዜ የጠበቃዎን ድጋፍ እንዳያገኙ ማገድ ይችላል። የተጠረጠሩበት ወንጀል ከአምስት አመት በማያንስ እስራት የሚያስቀጣ ከሆነ እገዳው ሊታደስ ይችላል።

# የትርጉም አገልግሎት ስለማግኘት

ፈረንሳይኛ የማይናገሩ ወይም የማይገባዎት ከሆነ ከክፍያ ነጻ በሆነ መልኩ በክስዎ ሂደትም ሆነ ከጠበቃዎ ጋር በሚነጋገሩበት ግዜ የትርጉም አገልግሎት የማግኘት መብት አሎት።

# ከእስር እንዲለቀቁ ስለመጠየቅ

በህግ ጥላ ስር የሚቆዩበት ግዜ እንዲራዘም ሊወሰን ፍርድ ቤቱ በሚቀመጥበት ግዜ፤ ግዜው እንዳይራዘም እና ከእስር እንዲለቀቁ ያስችላል የሚሉትን ምክንያት ለጠቅላይ አቃቤ ህጉ ወይም ጉዳዩ ለሚመለከተው ዳኛ መንገር ይችላሉ።

# ከጉዳይዎ ጋር የሚገናኙ የተወሰኑ ነገሮችን የማግኘት መብት

በእርስዎ ወይም በጠበቃዎ ጥያቄ መሰረት እና በህግ ጥላ ስር የሚቆዩበት ግዜ ከመራዘሙ በፊት የሚከተሉትን መጠየቅ ይችላሉ፡-

– በቁጥጥር ስር መዋልዎን የሚገልፅ መግለጫ

– የመረመርዎ ዶክተር የሰጠው የህክምና ሰርቲፊኬት

– የክስ ሂደትዎ-ጉባኤ

# አቃቤ ህጉን ስለማናገር

በቁጥጥር ከዋሉበት ግዜ አንድ አመት በኋላ መቀበልዎን በሚያረጋግጥ ድብዳቤ ወይም መቀበልዎን ለመዝገብ ቤት በማሳወቅ የክስዎን ፋይል ለማየት አቃቤ ህጉን መጠየቅ ይችላሉ።